የኢትዮጵያ መድኃኒት
አቅራቢ አገልግሎት

ማገልገል ክብር ነው

# መመሪያ ቁጥር 11202018

# በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት

# የቅድሚያ ውል የሚገባበት የመድኃኒት አቅርቦት ሥርዓት አፈጻጸም መመሪያ

ታህሳስ/2018

ጤና ተቋማት ለአገልግሎቱ የሚያቀርቡት የመድኃኒት ግዥ ጥያቄ ወቅታዊ፣ትክክለኛ ምጠና ላይ የተመሰረተ እና በበጀት የተደገፈ በማድረግ የግዥና ስርጭት መዘግየትን፣የመድኃኒት አቅርቦት እጥረትን እና ብክነትን በማስቀረት የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎችን መመለስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የመድኃኒት አቅርቦትን የቅድሚያ ውል በሚገባበት የአቅርቦት ስርዓት በመደገፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲቀንስ በማድረግ የአገልግሎቱን የአቅርቦት አቅም ማሳደግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የመሰረታዊ መድኃኒቶችን ፍላጎትና አቅርቦት አጣጥሞ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ለጤና ተቋማት ለማቅረብ እያጋጠመ ያለዉን ተግዳሮት ለመቅረፍ እና ከጤና መድህን ትግበራ ጋር ተያይዞ እየጨመረ የመጣውን የጤና አገልግሎት ፍላጎት ለማርካት የመድኃኒት አቅርቦትን በዘላቂነት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግና የህብረተሰቡን ጤና ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፤

በጤና ተቋማት ጥራት ያለው የመድኃኒት ምጠና ማከናወን የሚያስችል እና በተረጋገጠ በጀት ላይ የተመሠረተ ውል የመግባትና ግዥ የማከናወን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

አገልግሎቱ በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎትና ፈንድ ማቋቋሚያ በአዋጅ ቁጥር 1354/2017 አንቀጽ 24(2) እና 28(2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ **"የቅድሚያ ውል የሚገባበት የመድኃኒት አቅርቦት ሥርዓት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር** 1120/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፤

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "አዋጅ" ማለት የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት እና ፈንድ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1354/2017 ነው፡፡
2) **"አገልግሎቱ"** ማለት የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ነው፤
3) **"የጤና አስተዳደር"** ማለት የጤና ሚኒስቴር፣ የክልል ጤና ቢሮ፣ የዞን ጤና መምሪያ፣ የወረዳ ጤና ጽህፈት ቤት፣ የከተማ አስተዳደር ጤና መምሪያ፤ የክፍለ ከተማ ጤና ጽህፈት ቤትን ያካትታል፤
4) **"የቅድሚያ ውል የሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓት"** ማለት በበጀት በተደገፈና በመድኃኒት ፍላጎት ላይ በተመሠረተ መንገድ ጤና ተቋማት በቅድሚያ ከአገልግሎቱ ጋር በሚፈፅሙት ውል መሠረት የሚስተናገዱበት የአቅርቦትሥርዓት ነው፤
5) **"ባለድርሻ አካል"** ማለት ሚኒስቴሩን፤ የገንዘብ ሚኒስቴርን፤ የክልል ጤና ቢሮን፣ የዞን ጤና መምሪያን፣ ፤የከተማ አስተዳደር ጤና መምሪያን፣ የወረዳ ጤና ጽህፈት ቤትን፣ የጤና ተቋምን፣ የክልል፣የዞንና የወረዳ ፋይናንስ ቢሮን፣ የልማት አጋርን፣ የማህበረሰብ አቀፍ ጤና መድህንን፤ ባንኮችን እና ይሄን መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሚና ያላቸውን ሌሎች አካላትንም ያካትታል፡፡
6) በአዋጁ ላይ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሐረጎች በዚህም መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

3. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በማናቸውም የቅድሚያ ውል የሚገባበት የመድኃኒት አቅርቦት ሥርዓት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤

# <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ቅድሚያ ውል የሚገባበት የመድኃኒት አቅርቦት ሥርዓት</u>

4. <u>የቅድሚያ ውል የሚገባበት የመድኃኒት አቅርቦት ሥርዓት አፈጻጸም</u>

   1) ማንኛውም የጤና ተቋም የሚስተናገደው የቅድሚያ ውል የሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓት ውስጥ በተካተተው የመድኃኒት ፍላጎት ዝርዝር መሠረት ብቻ ይሆናል፤
   2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም፣ የቅድሚያ ውል በሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓት ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ መድኃኒት በጤና ተቋማት ተፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከአገልግሎቱ ጋር በሚደረግ ተጨማሪ ውል ሊስተናገድ ይችላል፤
   3) በዚህ አንቀጽ መሠረት አገልግሎቱ የቅድሚያ ውል የሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓትን ተከትሎ ጤና ተቋማት በቅድሚያ እንዲከፍሉ በማድረግ፣ በእጅ በእጅ ሽያጭ ወይምበዱቤ ውል መሰረት መድኃኒቶችን ለጤና ተቋማት ያቀርባል፡፡

5. <u>ጤና ተቋማት በቅድሚያ እየከፈሉ የሚስተናገዱበት ሁኔታ</u>

   1) ዝርዝር አፈጻጸሙ በአገልግሎቱ እና በጤና ተቋማቱ መካከል በሚፈጸመው የቅድሚያ ውል የሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓት ውል የሚወሰን ሆኖ አገልግሎቱ ጤና ተቋማት በሚያቀርቡት በበጀት የተደገፈ የመሠረታዊ መድኃኒቶች ፍላጎት ዝርዝር መሠረት የቅድሚያ ክፍያ እንዲከፍሉ በማድረግ ያቀርባል፤
   2) ቅድሚያ ክፍያ ለሚከፍሉ ጤና ተቋማት አገልግሎቱ የማበረታቻ ስርአት ይዘረጋል፤
   3) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም ጤና ተቋማት ለመድኃኒት መግዣ ያስያዙት በጀት በቅድሚያ ወደ አገልግሎቱ የሂሳብ ቋት እንዲገባ በማድረግ በቀረበላቸው መሠረታዊ መድኃኒት ልክ ሂሳቡ የሚወራረድበትን አሠራር ስርአት እንዲዘረጋ አገልግሎቱ ከገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ከሚመለከተው የክልል ፋይናንስ ቢሮ ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

6. <u>ጤና ተቋማት የእጅ በእጅ ሽያጭ የሚስተናገዱበት ሁኔታ</u>

   የቅድሚያ ውል በሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓት ዝርዝር ውስጥ ለተካተቱ መድኃኒቶች ጤና ተቋማት የእጅ በእጅ ሽያጭ የክፍያ አማራጭን መጠቀም ይችላሉ፤

7. <u>ጤና ተቋማት በዱቤ የሚስተናገዱበት ሁኔታ</u>

   1) ዝርዝር አፈጻጸሙ በአገልግሎቱ እና በጤና ተቋማቱ መካከል በሚፈጸመው የቅድሚያ ውል የሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓት የብድር ስምምነት የሚወሰን ሆኖ፣ በአዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 14 እና አንቀጽ 23 መሠረት ጤና ተቋማት የሚያቀርቡት በበጀት የተደገፈ የመሠረታዊ መድኃኒቶች ፍላጎትን ተከትሎ አገልግሎቱ መሠረታዊ መድኃኒቶችን በዱቤ ሊያቀርብ ይችላል፤

2) ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም አገልግሎቱ እንደአግባብነቱ ከገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ከክልል ፋይናንስ ቢሮዎች ጋር በሚያደርገው ስምምነት መሠረት ለጤና ተቋማቱ መሠረታዊ መድኃኒቶችን በዱቤ ካቀረበ በኋላ አስፈላጊ የሆኑ የሰነድ ማስረጃዎችን ለገንዘብ ሚኒስቴር ወይም ለክልል ፋይናንስ ቢሮዎች በማቅረብ የጤና ተቋማቱ ዕዳ ክፍያ በቀጥታ ወደ አገልግሎቱ የሂሳብ ቋት የሚተላለፍበትንና ሂሳቡ የሚወራረድበትን የአሠራር ስርአት እንዲዘረጋ በትብብር ይሰራል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ስለ አገልግሎቱ እና ጤና ተቋማት ኃላፊነት

### 8. የአገልግሎቱ ኃላፊነት

1) የቅድሚያ ውል በሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓት መሠረት የሚቀርቡ መድኃኒቶችን ዝርዝር በማዘጋጀት ለጤና አስተዳደር እና ለጤና ተቋም የማሳወቅ፤
2) የቅድሚያ ውል በሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓት መሠረት ለሚቀርቡ መድኃኒቶችወቅታዊ የገበያ ዋጋ ጥናት በማድረግ እና ግምታዊ የዋጋ ዝርዝርበማዘጋጀት ለጤና ተቋማት ተደራሽ የማድረግ፤
3) ጤና ተቋማት በየዓመቱ ለሚያቀርቡት በበጀት የተደገፈ የመድኃኒት ፍላጎት ዝርዝር ከጤና ተቋሙ ጋር ወይም አግባብነት ካለው ጤና አስተዳደር አካል ጋር ውል የመግባት፤
4) ዓመታዊ የጤና ተቋምን የመድኃኒት ፍላጎት በተገባው ውል መሰረት የማደራጀት፤
5) ጥራታቸው፣ ደህንነታቸው እና ፈዋሽነታቸው የተረጋገጠ መሠረታዊ መድኃኒቶችን በተገባው ውል መሰረት የማቅረብ፤
6) ጤና ተቋማት በሚያቀርቡት የአቅርቦት ፍላጎት ዕቅድ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በውሉ ላይ በሚቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መድኃኒት ለጤና ተቋም የማቅረብ፤
7) መድኃኒት ወደጠየቀው ጤና ተቋም ከመላኩ በፊት በውሉ በሚገለጸው መጣኔ መሰረት ከጠቅላላ ግምታዊ ዋጋ ጨምሮ ከተገኘ ጤና ተቋሙ ልዩነቱን እንዲከፍል ወይም የፍላጎት መጠኑን እንዲያስተካክል የማሳወቅ፤
8) ከጤና ተቋማት ወይም ከጤና አስተዳደር ጋር በሚገባው የውል ስምምነት መሰረት መድኃኒቶችን ጤና ተቋማት ድረስ የማድረስ፤
9) ጤና ተቋማት በገቡት ውል መሰረት መድኃኒት መውሰዳቸውን መከታተል እና አፈጻጸሙን በየሩብ ዓመቱ በመገምገም፤ ለሚመለከተው የጤና አስተዳደር የማሳወቅ፤
10) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ጤና ተቋም የቅድሚያ ክፍያ የፈጸመ ከሆነ አገልግሎቱ በውሉ መሰረት መድኃኒት የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

11) ለጤና ተቋማት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መስጠት፤ እንዲሁም የቴክኒካል ድጋፍ ስራዎች ላይ መሳተፍ፤

## 9. የጤና ተቋም ኃላፊነት

1) ጤና ተቋሙ የአከባቢውን የበሽታ ስርጭትና የአገሪቱን የመሰረታዊ መድኃኒቶች ዝርዝር መሰረት በማድረግ በጤና ተቋሙ ቅድሚያ የሚሰጣቸዉን የመድኃኒት ዝርዝር ያዘጋጃል፤ ያጸድቃል፤
2) በበጀት የተደገፈ ዓመታዊ ፍላጎትን በማዘጋጀት በጤና ተቋሙ ስራ አመራር ያጸድቃል፤ በጤና ተቋሙ የበላይ ሃላፊ ተፈርሞ ለአገልግሎቱና ለሚመለከተዉ ጤና አስተዳዳር በየዓመቱ እስከ ሚያዚያ ወር መጨረሻ ድረስ ይልካል፤
3) ጤና ተቋሙ የቅድሚያ ውል የሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓትን ተከትሎ ባሳወቀው የመድኃኒት ዝርዝር መሰረት ከአገልግሎቱ ጋር ውል ይፈራረማል ወይም በሚመለከተው ጤና አስተዳደር እንዲፈረም ያደርጋል፤
4) የቅድሚያ ውል በሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓት ፍላጎት ዕቅድ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የመጀመሪያውን ሩብ ዓመት እስከ ሐምሌ 15፣ የሁለተኛውን ሩብ ዓመት እስከ ጥቅምት 15፣ የሶስተኛውን ሩብ ዓመት እስከ ጥር 15 እና የአራተኛውን ሩብ ዓመት እስከ ሚያዚያ 30 ለአገልግሎቱ ማቅረብ አለበት፤
5) የውል ግዴታ የተገባለትን የመድኃኒት ፍላጎት ዝርዝር መጠን የመውሰድ ግዴታ፤
6) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ጤና ተቋሙ መድኃኒት ከመረከቡ በፊት ትክክለኛው ዋጋ ከጠቅላላ ግምታዊ ዋጋ በልጦ ከተገኘ ልዩነቱን የመክፈል ወይም የፍላጎት መጠኑን የማስተካከል፤
7) የቅድሚያ ውል በሚገባበት የመድሃኒት አቅርቦት ውል ስምምነቱ ላይ በተመለከተው የግዥ እቅድ መሰረት መድኃኒቶችን የመረከብ፤
8) የቅድሚያ ውል በሚገባበት የመድሃኒት አቅርቦት ውል መሰረት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ በወቅቱ የሚጠበቅበትን ክፍያ የመፈጸም፤
9) የቅድሚያ ውል የሚገባበት የመድኃኒት አቅርቦት ሥርዓት አፈጻጸምን በየሩብ አመቱ ለጤና አስተዳደር አካላት የማሳወቅ፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 10. ክትትልና ግምገማ

1) አገልግሎቱ የቅድሚያ ውል የሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓትን ውጤታማነት ለመገምገም የሚያስችሉ የአፈጻጸም መለኪያዎችን ይቀርጻል፤
2) የቅድሚያ ውል የሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓት በአገልግሎቱ የዕቅድ ክትትል እና ግምገማ ማዕቀፍ ውስጥ ተካቶ በየሩብ ዓመቱ እየተገመገመ በግምገማ ውጤቱ ላይ የተመሠረቱ የማሻሻያ ዕርምጃዎች ይወሰዳሉ፤

### 11. የቅድሚያ ውል ስለሚፈረምበት ሁኔታ

1) የቅድሚያ ውል የሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓት ውል በጤና አስተዳደር ወይም በጤና ተቋማት ደረጃ ሊፈረም ይችላል፤
2) የቅድሚያ ውል የሚገባበት የአቅርቦት ሥርዓት ውል የሚፈጸመው ከሰኔ 1 እስከ ሰኔ 30 ድረስ ይሆናል፡፡

### 12. መሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ጸድቆ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ቀደም ብሎ የተፈጸመ የቅድሚያ ውል የተገባበት የመድኃኒት አቅርቦት ውል በተጀመረው አግባብ የሚፈጸምይሆናል፡፡

### 13. የተሻሩና ተፈጻሚ የማይሆኑ ህጎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

### 14. የመመሪያው ተፈጻሚነት

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በአገልግሎቱ ድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ታህሳስ/2018፣ አዲስ አበባ**

**አብዱልቃድር ገልገሎ (ዶ/ር)**

**የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር**